# ፖሊሲ

## የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ

**ተዛማጅ ርዕሶች፡-** ACA, ACF-RA, ACI, ACI-RA, GCC-RA, IGP-RA, JFA, JFA-RA, JGA-RB, JGA-RC, JHC, JHC-RA, JHF, JHF-RA

**ኃላፊነት የሚመለከታቸው ጽ/ቤቶች፡-** የዲስትሪክት ኦፐሬሽንስ ጽ/ቤት ኃላፊ፣ የት/ቤት ድጋፍ እና ማሻሻያ ቢሮ ዋና ኃላፊ

## የተማሪዎች ጾታዊ በደል እና ጾታን መሰረት ያደረገ ትንኮሳ

A. ዓላማ

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት ውስጥ ጾታዊ በደልን እና ፆታን መሰረት ያደረገ ትንኮሳን ለመከልከል።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች እና ተማሪዎች ጾታዊ በደሎችን እና ጾታን መሰረት ያደረጉ ትንኮሳዎችን እንዲያውቁ፣ እንዲረዱ እና ሪፖርት እንዲያደርጉ ለመርዳት የተነደፉ የትምህርት መርሃ ግብሮች እንዲዘጋጁ ኃላፊነት ለመስጠት።

የጾታዊ በደል እና ጾታን መሰረት ያደረገ ትንኮሳ ቅሬታዎችን ለመፍታት ውጤታማ የአሠራር ሥርዓቶችን ማዕቀፍ ለማበጀት።

B. ጉዳዩ

1. የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ (ቦርድ) በማንኛውም ሁኔታ በትምህርት ፕሮግራሞቹ እና በእንቅስቃሴዎቹ/በተግባሮቹ፣ ወይም በንብረቱ ውስጥ ማንኛውንም ዓይነት የተማሪዎች ጾታዊ በደልን ወይም ጾታን መሰረት ያደረገ ትንኮሳን አይታገስም። ለዚህ ፖሊሲ ዓላማ፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት ማለት ማንኛውም ትምህርት ቤት ወይም መሬትን ጨምሮ ሌሎች MCPS ይዞታ ላይ የሚገኙ መገልገያዎች (ፋሲሊቲዎች)፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አውቶቡሶች እና ሌሎች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተሽከርካሪዎች እና በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሚደገፍ-ፕሮግራም ወይም እንቅስቃሴና ቦታዎችን ጭምር የሚያጠቃልል ሲሆን፥ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሃላፊነት ሥር የሚገኙ ግለሰቦች የተሳተፉባቸው ክስተቶች እና ተከስቷል ተብሎ የሚጠረጠር የትንኮሳ ሁኔታ ማለት ነው።

2. ተማሪዎች፣ ሠራተኞች፣ እና ሶስተኛ ወገኖች ጾታን መሰረት ካደረገ ትንኮሳ ነፃ የመሆን መብት አላቸው። ቦርዱ ሁሉም ሰው ከሁሉም ዓይነት ጾታዊ በደል እና ጾታን መሰረት ያደረገ ትንኮሳ ነፃ የሆነበትን የትምህርት አካባቢ ለመፍጠር እና ለመጠበቅ፥ እናም ይህንን ፖሊሲ የሚጥሱ ባህሪያትን ለመከላከል፣ ለማረም እና የስነምግባር ዲሲፕሊን እርምጃ ለመውሰድ ቁርጠኛ ነው።

3. ትርጓሜዎች

   a) ጾታዊ ግብረገብን ወይም ህግን የጣሰ ተግባር

      (1) ጾታዊ በደል በአንድ ግለሰብ ወይም ቡድን ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ጾታ፣ የጾታ ዝንባሌ፣ የጾታ ማንነት፣ የሥርዓተ-ፆታ መግለጫ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣

የእርግዝና/የወላጅነት ሁኔታ፣ እና/ወይም በጾታ ላይ የተመሠረተ የወንድነት ወይም የሴትነት ጽንሰ-ሀሳቦችን መሠረት በማድረግ በግለሰብ ላይ ወይም በአንድ የተወሰነ ቡድን ላይ ያተኮረ የቃል፣ የጽሑፍ፣ ወይም አካላዊ የጾታ ትንኮሣ/ጥቃት የማድረስ ባህሪን ያጠቃልላል እና ምግባሩ ተቀባይነት የሌለው ከመሆኑም በላይ የሚከተሉትን መስፈርቶች ያሟላ ከሆነ፡-

(a) ለድርጊቱ ፈቃድን መስጠት ወይም ድርጊቱን አለመቀበል የሚገለጸው በግልፅ ወይም በተዘዋዋሪ በግለሰብ ትምህርት ወይም በቃል በሚገለጽ ሁኔታ፣ ወይም በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሥራ እንቅስቃሴ/ተግባር ወይም ፕሮግራም ውስጥ በመሳተፍ፣ ወይም

(b) ለምግባሩ ፈቃድን መስጠት ወይም ምግባሩን አለመቀበል የግለሰብን ትምህርት በሚነኩ ውሳኔዎች ወይም በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) እንቅስቃሴ ወይም ፕሮግራም ላይ ለመሳተፍ እንደ መሠረት ሆኖ የሚያገለግል ከሆነ፣ ወይም

(c) ምግባሩ በግለሰቡ(ቧ) ትምህርት ወይም በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) እንቅስቃሴ/ተግባር ወይም ፕሮግራም ውስጥ በመሳተፍ ላይ የሚያስፈራራ/ስጋት ላይ የሚጥል፣ የማይመች/አድሎዎ ያለበት ወይም አስፀያፊ አካባቢን የመፍጠር ዓላማ ወይም ውጤት ካለው፣

(d) ምግባሩ በግለሰብ ትምህርት፣ ወይም በ MCPS እንቅስቃሴ/ተግባር ወይም ፕሮግራም ውስጥ የመሳተፍ ችሎታን ያለአግባብ የሚያስተጓጉል ከሆነ፤ እና

(2) ምግባሩ የግለሰቡ(ቧ)ን ትምህርት ወይም በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) እንቅስቃሴ/ተግባር ወይም ፕሮግራም ውስጥ የሚያደርገውን/የምታደርገውን ተሳትፎ የሚመለከቱ፣ ስምምነቶችና ውሎችን፣ ሁኔታዎችን ወይም መብቶችን በሚቀይር ሁኔታ ከባድ ወይም የተስፋፋ ከሆነ።

(3) ምግባሩ በቃላት/በንግግር፣ንግግር አልባ በሆነ መንገድ፣ በጽሑፍ ወይም በኤሌክትሮኒክ መንገድ ሊፈጸም ይችላል።

b) ጾታን መሰረት ያደረገ ትንኮሳ

(1) ጾታን መሰረት ያደረገ ትንኮሳ ተደርጎ የሚቆጠር ድርጊት 1972 የትምህርት ማሻሻያዎች ታይትል IX እና በአፈጻጸም ደንቦቹ እንዲሁም ክፍል (ታይትል IX) 42 U.S.C. Section 1983 ጭምር በዩ.ኤስ የትምህርት ዲፓርትመንት እንደተተረጎመው የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪ ከሚከተሉት አንዱን ወይም ከዚያ በላይ ካጋጠመው/ካጋጠማት በሌሎች የሲቪል መብቶችና ሕጎች መሠረት ሊተገበር ይችላል።

(a) አንድ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኛ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) እርዳታን፣ ጥቅማጥቅምን፣ ወይም አገልግሎትን ለመስጠት የግለሰቡን(ቧን) ባልተፈለገ ወሲባዊ ድርጊት ውስጥ መሳተፍን እንደ ቅድመ ሁኔታ መጠየቅ።

(b) በአጠቃላይ ሁኔታ ላይ በመመስረት፣ በግላዊ እና በተጨባጭ ሁኔታ አፀያፊ እና አንድ ሰው በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የትምህርት

ፕሮግራም ወይም እንቅስቃሴ/ተግባር ውስጥ የመሳተፍ ወይም ከትምህርት ፕሮግራም ወይም እንቅስቃሴ/ተግባር የመጠቀም ችሎታን በሚገድብ መልኩ በጣም ከባድ ወይም የተስፋፋ ያልተፈለገ ጾታ-ተኮር ምግባር።

(c) በፌዴራል ሕግ እንደተገለጸው "ጾታዊ ጥቃት"፥ "የፍቅር ጓደኛን ማጥቃት"፥ "የቤት ውስጥ ጥቃት" ወይም "እያሸመቁ-እያደቡ ማሳደድ" ማለት ነው።

(2) MCPS ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ፕሮግራም ወይም እንቅስቃሴ/ተግባር ውጭ ወይም ከዩናይትድ ስቴትስ ውጭ ለተፈጠረው ምቹ ያልሆነ/አድልዎ ላለበት አካባቢ አስተዋፅዖ ያደረገ ምግባርን ጨምሮ፣ ነገር ግን በዚ ብቻ ሳይወሰን፣ በፕሮግራሙ ወይም በተግባሮቹ ውስጥ ሁሉንም ጾታዊ አድልዎ ወይም ያልተፈለገ ጾታዊ ግንኙነትን መሰረት ያደረገ ምግባርን ትኩረት በመስጠት ይፈታል።

(3) በፌዴራል ሕግ በተገለጸው መሠረት በዝርዝር የታወቀ ጾታን መሰረት ያደረገ የትንኮሳ ተግባርን የማያሟላ ምግባር በቦርድ ፖሊሲ JHF፣ ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ፣ ወይም ማስፈራራት መሠረት ምርመራ እና ተግሣጽ የሚያሰጥ ጾታዊ በደል ሊሆን ይችላል፣ MCPS የተማሪ የስነምግባር ኮድ፣ እና MCPS የሰራተኛ ስነምግባር ኮድ.

c) እንደ ጾታዊ በደል ወይም ጾታዊ ትንኮሳ ሊቆጠር የሚችል ድርጊት የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፤ ነገር በእነዚህ ብቻ አይወሰንም፦ አፀያፊ ቀልዶችን፣ ስድቦችን፣ማንጓጠጦችን ወይም የስም አጠራርን፣ አካላዊ ጥቃቶችን ወይም ማስፈራሪያዎችን፣ ማሾፍን ወይም ስድቦችን ወይም ማዋረድን፣ አስጸያፊ ቁሳቁሶችን ወይም ስዕሎችን ሊያካትት ይችላል።

d) ሶስተኛ ወገን ማለት፥ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኛ ወይም ተማሪ ያልሆነ(ች) MCPS የሥራ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የሚሳተፍ/የምትሳተፍ ወይም MCPS ንብረት ላይ የሚገኝ/የምትገኝ እና በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ስልጣን ወይም ቁጥጥር ያልተገደበ(ች) ማንኛውም ሰው ነው፥ ይኼውም፦ MCPS ንብረት ላይ መስተጋብር ያላቸው ሻጮች፣ ተቋራጮች፣ አሰልጣኞች፣ በጎ ፈቃደኞች፣ አማካሪዎች እና ሌሎች ሰራተኞች እና/ወይም ተማሪዎች ናቸው።

C. **አቋም**

1. የፖሊሲ ጥሰቶች የስቴት ወይም የፌዴራል ሲቪል እና/ወይም የወንጀል ሕጎችን የሚጥሱ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ይህ ፖሊሲ የሚመለከተው እያንዳንዱ ሰው የወንጀል ቅጣቶችን የሚያስከትል መሆኑን ስለ ድንጋጌዎቹ በማሳወቅ ረገድ የት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት የተቻለውን ሁሉ እንዲያደርግ/እንድታደርግ መመርያ ተሰጥቷል።

2. ይህ ፖሊሲ ለሁሉም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪ ወሲባዊ ትንኮሳ ክስተቶች ተፈጻሚ ይሆናል። በተማሪዎች፣በሠራተኞች ወይም በሦስተኛ ወገኖች የተፈጸሙ ክስተቶችን ይመለከታል/ይፈታል።

3. ጾታን መሰረት ያደረገ ትንኮሳ በማንኛውም ሰዎች መካከል የአንድ ጊዜ ክስተት ወይም ተደጋጋሚ ክስተት ሆኖ ሊከሰት ይችላል።

4. የሪፖርት እና ድጋፍ እርምጃዎች

a) ፆታዊ በደል ወይም ፆታን መሰረት ያደረገ ትንኮሳ ያጋጠማቸው ወይም የተመለከቱ ተማሪዎች፣

ወይም የእነሱ ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ለዳይሬክተራቸው ወይም ለሌላ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኛ ይሄን አይነቱን ድርጊት ማመልከት አለባቸው፣ ያሳወቁትም ግለሰብ ሪፖርት በማደርግ እና በምርመራ ሂደቶች ላይ ምን መደረግ እንዳለበት ይመራቸዋል እንዲሁም ማግኘት የሚችሉትን ሌሎች የድጋፍ እርምጃዎችን ያሳውቋቸዋል። እንዲሁም "Title IX sex-based harassment reporting email drop box" ጾታን መሰረት ያደረገ ትንኮሳን ሪፖርት ማድረጊያ የኢሜል አድራሻ TitleIX@mcpsmd.org ላይ ሪፖርት ማድረግ ይችላል።

b) ፆታዊ በደል ወይም ፆታን መሰረት ያደረገ ትንኮሳ ሲከሰት፣ ሁሉም የተሳተፉ አካላት ማግኘት ስለሚችሉት የድጋፍ እርምጃዎች እንዲያውቁ ይደረጋል። የድጋፍ እርምጃዎች የምክር አገልግሎት፣ የግዜ ገደቦችን ማራዘም ወይም ሌላ ከኮርስ ጋር የተዛመዱ ማስተካከያዎች፣ የትምህርት ክፍል መርሃ ግብሮችን ማሻሻል፣ ወይም ችግሩ በተፈጠረባቸው ወገኖች መካከል ባለው ግንኙነት ላይ ገደቦችን ማድረግ የመሳሰሉትን ያካትታል፣ ነገር ግን በዚህ ብቻ አያበቃም።

c) ጾታዊ በደልን ወይም ጾታን መሰረት ያደረገ ትንኮሳን በቃል ወይም በጽሑፍ ሪፖርት በሚያደርግ ሰው ላይ፣ ወይም በምርመራ ተካፋይ ወይም ተባባሪ በሆነ ግለሰብ ላይ የበቀል እርምጃን መውሰድን ቦርዱ ይከለክላል።

5. ምርመራ

በተማሪዎች፣ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሠራተኞች፣ በኮንትራክተሮች፣ በሥራ ተቋራጮች፣ ወይም በበጎ ፈቃደኞች በተማሪዎች ላይ የተፈጸሙ ጾታዊ በደሎች ወይም ጾታን መሰረት ያደረጉ ትንኮሳዎች በሙሉ ከተማሪዎች ደህንነት እና ስርዓት አስከባሪዎች ጋር በመተባበር እና በስቴትና በፌዴራል ሕጎች መስፈርቶች መሠረት በርዕሰ መምህሩ/ሯ ወይም በተወካይ ምርመራ ይደረግባቸዋል።

## D. የሚፈለጉ ውጤቶች

1. ሁሉም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች እና ተማሪዎች ጾታዊ በደልን ወይም ጾታን መሰረት ያደረገ ትንኮሳ ተብሎ ሊወሰድ የሚችል ተገቢ ያልሆነ ወሲባዊ ምግባርን በሁሉም መልኩ እንዲያውቁ/እንዲለዩ ግንዛቤ ይሰጣቸዋል/ተሰጥቷቸዋል።

2. ሁሉም ተማሪዎች እና ሰራተኞች ጾታዊ በደል ወይም ጾታን መሰረት ያደረገ ትንኮሳን ሪፖርት እንዲያደርጉ ተፈቅዶላቸዋል።

3. ሪፖርት ስለማድረግ፣ ስለ ምርመራ፣ ምላሽ ስለመስጠት እና የድጋፍ እርምጃዎችን ስለመውሰድ ውጤታማ እና ሕጋዊ እርምጃዎች ተግባራዊ ይሆናሉ።

4. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች፣ ሠራተኞች፣ እና ሶስተኛ ወገኖች ጾታን መሰረት ካደረገ ትንኮሳ ነፃ በሆነ አካባቢ ይማራሉ፥ ይሠራሉ።

## E. የአፈጻጸም ስልቶች

1. የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት፦

a) የዚህን ፖሊሲ እና ተዛማጅ የፌዴራል እና የስቴት ህጎችን እና ደንቦችን አፈፃፀም ለማስተባበር Title IX አስተባባሪ መሾም፤

b) Title IX ድንጋጌ መሠረት ለሚቀርቡት ቅሬታዎች የምርመራ ሂደቶችን ጨምሮ አፋጣኝ እና

ፍትሃዊ መፍትሄ ለመስጠትና እንደ አስፈላጊነቱ የድጋፍ እርምጃዎችን ለመውሰድ Title IX ድንጋጌ ጋር በሚጣጣም መልኩ ይህንን ፖሊሲ ለመተግበር ደንቦችን ማዘጋጀት፤

c) ጾታዊ በደልን ወይም ጾታን መሰረት ያደረገ ትንኮሳን የሚከለክሉ ይህንን ፖሊሲ እና ተዛማጅ የፌዴራል እና የስቴት ህጎችን ለተማሪዎች እና ለወላጆች/አሳዳጊዎች ማስተማር፥ እንዲሁም እንደ ማስታወቂያዎች፣ በራሪ አጫጭር ጽሑፎች፥ የማመልከቻ ቅጾች፣ ኮንትራቶች እና ሌሎች ግንኙነቶችን የሚዘረዝሩ መረጃዎችን በሰፊው በማሰራጨት ተማሪ እንዴት ሪፖርት ማቅረብ ወይም እርዳታ ማግኘት እንደሚቻል ማስተማር፤

d) ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሠራተኞች ይህንን ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችልና የሚደግፍ ሙያዊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠት፤

(1) የዚህን ፖሊሲ ተገቢ አፈፃፀም ለማረጋገጥ ለሁሉም ሠራተኞች ዓመታዊ ሥልጠና መስጠት፥ እና

(2) ሀላፊነት ለተሞላበት ባህሪ እና ተገቢ ለሆነ ምግባር ግልጽ የሆኑ መመዘኛዎችን የያዘ የሥነ ምግባር ደንብ እና ሌሎች መመሪያዎችን ለተማሪዎች፣ ለሠራተኞች እና በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት ውስጥ ለሚሠሩ ለሌሎች ሰዎች መስጠት፣ እና

e) የሜሪላንድ ሕግ በሚጠይቀው መሠረት ለሁሉም ተማሪዎች አጠቃላይ የጤና ትምህርት ማስተማሪያ መርሃ ግብርን ተግባራዊ ማድረግ፥ እና

f) በትምህርት ቤት፣ በስራ ቦታ፣ እና በማህበራዊ ቦታዎች ተገቢ ያልሆኑ የወሲባዊ ጫናዎችን የሚቀንሱ ባህሪያትን እና አመለካከቶችን ለማዳበር ተማሪዎችን ከጾታዊ ጥቃት እና ጾታን መሰረት ካደረገ ትንኮሳ ጋር የተገናኙ ጉዳዮችን ለማስተማር፣ እንደአስፈላጊነቱ፣ ሌሎች እድሎችን መጠቀም።

2. ይህንን መመሪያ የሚጥስ ማንኛውም ተማሪ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የተማሪ ስነምግባር ህግ መሰረት ለፈጸመ(ች)ው ጥቃት ተገቢ ምላሽ የሚሰጥ የዲሲፕሊን እርምጃ ይወሰድበ(ባ)ታል።

3. በማንኛውም ጊዜ፣ ጾታዊ ትንኮሳን ጨምሮ ነገር ግን በዚህ ብቻ ሳይወሰን Title IX ጥሰት ተፈጽሟል የሚል/የምትል ተማሪ፣ ወደ "U.S. Department of Education's Office for Civil Rights (OCR)" ቅሬታ ማቅረብ ትችላለች/ይችላል። አንድ ተማሪ በዩ.ኤስ. የትምህርት ዲፓርትመንት የሲቪል መብቶች ቢሮ ቅሬታ ከማቅረቡ/ቧ በፊት ወይም ካቀረበ/ች በኋላ ወደ MCPS አቤቱታ ማቅረብ አይጠበቅበ(ባ)ትም።

U.S. Department of Education, Office of Civil Rights ዩ.ኤስ. የትምህርት ዲፓርትመንት የሲቪል መብቶች ቢሮ
OCR ኤሌክትሮኒክስ የቅሬታ ማቅረቢያ ቅጽ
(http://www.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html)፣ ወይም
U.S. Department of Education, Office for Civil Rights
Lyndon Baines Johnson Department of Education Building
400 Maryland Avenue, SW
Washington, DC 20202-1100

4. በማንኛውም ጊዜ፣ወሲባዊ ባህርይ እንዳላቸው የሚጠረጠሩ ወንጀሎችን ተማሪ ለህግ አስከባሪዎች በቀጥታ

ሪፖርት ማድረግ ወይም አቤቱታ ማቅረብ ይችላል-ትችላለች፡-

Montgomery County Police Department
Special Victims Investigation Division
100 Edison Park Drive
Gaithersburg, MD 20878

ወይም፣ the Safe Schools Maryland Tip Line, 1-833-MD-B-SAFE

**F. ግምገማ እና ሪፖርት**

1. የትምህርት ቤቶች ሱፐሪኢንተንደንት በዚህ ፖሊሲ ድንጋጌ መሠረት ሪፖርት የተደረጉ ጾታን መሰረት ያደረጉ ትንኮሳዎችን እና የጾታዊ በደል ክስተቶችን እንዲሁም ሌሎች ስነ ስርአት የማክበር ግድፈቶችን በሚመለከት በየሩብ ዓመቱ ለቦርዱ ሪፖርት ያደርጋል/ታደርጋለች። የክስተቱ ሪፖርቶች ካለፈው ሩብ ዓመት ጀምሮ የተፈጸሙ ተከታታይ ክስተቶችን መረጃዎች ማካተት አለባቸው። የስነሥርአት አለማክበር ሪፖርቱ ቅሬታ፣ እና የእርምጃ አወሳሰድ ሂደት ግምገማዎችን፣ እና ማሻሻያዎችን ያካትታል፥ ስልጠና የተሰጠበት ስታቲስቲክስ እና መርሃ ግብሮች፣በሁሉም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ትምህርት ቤቶች፣ ቢሮዎች፣ እና የስራ ቦታዎች ላይ የተደረገ የስራ አካባቢ አውድ ግምገማ፤ እና ለዚህ ፖሊሲ ስኬታማ ትግበራ ጠቃሚ የሆኑ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የታቀዱ ወይም የሚከናወኑ ሌሎች ተግባራትንም ያጠቃልላል።

2. ይህ ፖሊሲ በቦርዱ የፖሊሲ ግምገማ ሂደት መሰረት ቀጣይነት ባለው መልኩ ይገመገማል።

**ተዛማጅ ምንጮች፡-** Title VII of the Civil Rights Act of 1964, as amended, 42 U.S.C. §2000e et seq; Title IX of the Education Amendments of 1972, 20 U.S.C. §1681 et seq; 29 C.F.R. §1604,11; 34 C.F.R 106.30(a); Annotated Code of Maryland, Education Article, §6-104, §6-113, §6-113.2, §7-303.1, §7-424, §7-424.1, §7-424.3, and §11-60; Annotated Code of Maryland, State Government Article, Title 20, Human Relations; Code of Maryland Regulations §13A.12.05.02; Student Code of Conduct in MCPS; MCPS Employee Code of Conduct; MCPS Guidelines for Student Gender Identity

**የዚህ ፖሊሲ ታሪክ፡-** የፀደቀበት ውሳኔ ቁ. 837-92፥ ኖቬምበር 23, 1992 በውሳኔ ቁጥር 466-96, ጁን 24, 1996 የተሻሻለው በውሳኔ ቁ. 322-21 ጁን 29, 2021 የተሻሻለው በውሳኔ ቁ. 465-24, ኦክቶበር 10, 2024 ነው።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ማድረግን ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (ግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም ህገ-መንግሥታዊ ጥበቃ የተደረገላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትኃዊነት፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለማስፈን እና ለማዳበር/ለመንከባከብ ሲካሄድ የቆየውን ጥረት ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምድ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ "የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA" ይመልከቱ:- "ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ለሴት ልጆች በስካውትነት እና በሌሎች የወጣት ቡድኖች ለመመደብ እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።

A. በሜሪላንድ ስቴት ፖሊሲ መሠረት ሁሉም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና የትምህርት ቤት ፕሮግራሞች የሚከተሉትን ድንጋጌዎች በማክበር መንቀሳቀስ አለባቸው:-
  (1) 1964 የፌደራል ሲቪል መብቶች ህግ አንቀጽ VI፣ እና
  (2) በሜሪላንድ ኮድ የትምህርት ደንብ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 7፣ ይኼውም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች:-
    (a) በዘር፣ በጎሳ፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ በብሔር፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በፆታዊ ሁኔታ፣ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት፣ ወይም የአካል ጉዳተኝነት ምክንያት፣ አሁን ባሉት ተማሪዎች ላይ፣ የወደፊት ተማሪዎች ላይ፣ ወይም የአሁን ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ላይ አድልዎ ማድረግ የተከለከለ ነው፣
    (b) በአንድ ግለሰብ ዘር፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ ምክንያት የወደፊት ተማሪዎችን መመዝገብ እምቢ ማለት፣ የአሁኑን ተማሪዎች ማባረር፣ ወይም ከአሁን ተማሪዎች፣ የወደፊት ተማሪዎች ወይም የአሁኑ ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆችን ወይም አሳዳጊዎችን የሃይማኖት፣ የጾታ፣ የዕድሜ፣ የብሔር፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የፆታ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት ወይም የአካል ጉዳት፣ የመሳሰሉትን ምክንያት በማድረግ መብቶችን መከልከል፣ ወይም
    (c) የትምህርት ውጤቱ(ቷ) ምንም ይሁን ምን መርሃ ግብሩ ወይም ትምህርት ቤቱ በተማሪው(ዋ) ላይ አድሎአዊነትን ፈጽመዋል የሚል ቅሬታ ባቀረበ(ች) ተማሪ ወይም ወላጅ ወይም አሳዳጊ ላይ ቅጣት ማድረግ፣ ወይም ማንኛውንም ሌላ የበቀል እርምጃ መውሰድ የተከለከለ ነው**

እባክዎን የግንኙነት መረጃ እና የፌዴራል፣ የስቴት፣ ወይም የአካባቢ መረጃ ይዘትን በተመለከተ መስፈርቶቹ በዚህ ሰነድ እትም ላይ ተለውጠው ሊሆን ይችላል፥እና በወቅታዊ መረጃ እንደተተካ ልብ ይበሉ። በዚህ ውስጥ የተካተቱትን መግለጫዎች እና ማመሳከሪያዎችን ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት እባክዎን ይህንን በይነመረብ ይመልከቱ:- www.montgomeryschoolsmd.org/info/nondiscrimination

| በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው:-*** | በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ላይ ስለሚደርስ መድልዎ ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው:-*** |
|---|---|
| Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>15 West Gude Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| SWC@mcpsmd.org | Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| 1973 የተሃድሶ ድእንብ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የመገልገያ/አኮሞዴሽን/ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው:- | በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የመገልገያ/የአኮሞዴሽን/ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው:- |
| Section 504 Coordinator<br>Office of School Support and Improvement<br>Well-Being and Student Services<br>850 Hungerford Drive, Room 257, Rockville, MD 20850<br>240-740-3109 \| 504@mcpsmd.org | ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| ታይትል IX ስር ስለ ፆታዊ መድልዎ፣ ጾታዊ ትንኮሳን ጨምሮ፣ በተማሪዎች ላይ ወይም በሰራተኞች ላይ ስለሚደረግ ጥቃት ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው:-*** | |
| Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>15 West Gude Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| TitleIX@mcpsmd.org | |

*ይህ መግለጫ ከተሻሻለው የፌዴራል የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ህግ ጋር የተጣለጠ ነው።
**ይህ መግለጫ የሜሪላንድ ዝርዝር ደንብ/ኮድ አንቀጽ 13A.01.07. ጋር የተጣለጠ ነው።
***የመድሎአዊነት ቅሬታዎችን ለሚከተሉት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል:-

U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; Agency Equity Officer, Office of Equity Assurance and Compliance, Office of the Deputy State Superintendent of Operations, Maryland State Department of Education, 200 West Baltimore Street, Baltimore, MD 21201-2595, oeac.msde@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, ወይም www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቋንቋ/ፎርማት ማግኘት ካስፈለገ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር:- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay) ወይም PIO@mcpsmd.org በመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤትን በዚህ ኤሜይል ወይም በስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services ስልክ ቁጥር 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, oወይም MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org

ሀምሌ 2024